# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 140461

መስከረም 29 ቀን 2010ዓ.ም

ዳኞች:-

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች:- አቶ ንጉሴ ዘርይሁን -ቀረቡ

ተጠሪ:- የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን -ወኪል አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ:- የስራ ክርክርን ይመለከታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች በሲቪልሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 044/09 ጥር 30 ቀን 2009ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 138065 መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይህንኑ ፍርድ በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

በመዝገቡ ከተያያዙት የውሳኔ ግልባጮች መረዳት እንደሚቻለው የአሁኑ ተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ከድሲፕሊን ኮሚቴው የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ተመልክተው አመልካች ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ ባልታወቀ ምክንያት በስራ ገበታ ላይ አልተገኙም በማለት ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸው እንዲቋረጥ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ቅሬታውም በአጭሩ ከተጠሪ ፍቃድ ወስጄ እረፍት ላይ እያለሁ የጫማ ኢንፌክሽን እና የቁርጭምጭሚት ውልቃት ደርሶብኝ በህክምና ላይ መሆኔን አሳውቄ ተጠሪም እስከ ህዳር 30 ቀን 2007ዓ.ም ድረስ ደመወዝ የከፈለኝ እና በህመሜም ምክንያት

የመ/ቤቱን ማስታወቂያ መከታተል የማልችል መሆኔ እየታወቀ ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሌ እንዲቋረጥ መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ቢያዘውም ባለመቅረቡ የመከራከር መብቱ ታልፎ የይግባኝ ባይን ክርክር ሰምቶ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያስተላለፈው የስራ ስንብት ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምሮ አመልካች ከደረሰባቸው የጫማ ኢንፌክሽን እና የቁርጭምጭሚት ውልቃት አዳማ ሆስፒታል ታክመው ከህዳር 3/2007 እስከ ሚያዝያ 30/2007ዓ.ም ድረስ በህክምና ፍቃድ ላይ የነበሩ መሆናቸው፣ ሰኔ 2 ቀን 2007ዓ.ም ቁርጭምጭሚታቸው በብሎን ታስሮ እስከ ታህሳስ 6 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ በህክምና ክትትል ላይ የነበሩ መሆኑን፣ ነሀሴ 10 ቀን 2008ዓ.ም በተጻፈ አመልካች የስኳር ታማሚ እና በሶዶ ሆስፒታል ለ3ኛ ጊዜ ቀዶ ህክምና የተደረገላቸው እና በአዳማ ሆስፒታል በክትትል ላይ የሚገኙ መሆናቸውን እና መጋቢት 1ቀን 2008ዓ.ም እና ሚያዝያ 3ቀን 2008ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ከደረሰባቸው የጤና መታወክ የተሻላቸው መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ወደ ስራ እንዲያሰማራቸው ለተጠሪ የጠየቁበት ደብዳቤ እና ተጠሪ ሰኔ 2ቀን 2007 ዓ.ም. የጻፈላቸው የስንብት ደብዳቤ ግንቦት 23/2008ዓ.ም የደረሳቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ የአመልካችን የስራ ውል ለማቋረጥ ምክንያት ያደረገው አመልካች በስራ ገበታቸው አልተገኙም በማለት ታህሳስ 27/2007 እና ጥር 7/2007 ተደጋጋሚ ማስታወቂያ በማውጣት ሰኔ 2/2007 ዓ.ም በተጻፈ ከታህሳስ 17/2007ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሉ መቋረጡን የገለጸበት ደብዳቤ ግንቦት 23/2008ዓ.ም እንዲደርሳቸው በማድረግ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት አትቶ እና የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 42/5ን ጠቅሶ አመልካች በህክምና ላይ የነበሩ መሆናቸውን ለተጠሪ እንደገለጹ እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 42(3) መሰረት ለመጀመሪያዎቹ 3 ወራት ከሙሉ ደሞዝ ጋር፣ ለቀጣዩ 3 ወራት ከግማሽ ደሞዝ ጋር፣ ለመጨረሻዎቹ 2 ወራት ያለ ደሞዝ ተጠሪ ፍቃድ መስጠት ያለበት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም

አመልካች ከስራ ገበታቸው ከቀሩበት ከታህሳስ 17/2007ዓ.ም ጀምሮ 8 ወር ሲቆጠር እስከ ነሀሴ 16 ቀን 2007ዓ.ም ድረስ ተጠሪ አመልካችን የመጠበቅ ግዴታ ነበረበት በማለት ደምድሞ ከታህሳስ 17/2007ዓ.ም ጀምሮ አመልካች በነበራቸው የህክምና ፍቃድ ምክንያት ለመጀመሪያዎቹ 3ወራት እና ቀጥሎ ላሉት 3 ወራት በአዋጁ መሰረት ክፍያ እንዲፈጽም፣ አመልካች የጠየቁት የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ላልተሰራ ጊዜ የሚከፈል አይደለም በማለት ውድቅ በማድረግ አመልካች ወደስራ ልመለስ ጥያቄንም በተመለከተ አመልካች ወደስራ ልመለስ በማለት ጥያቄ ያቀረቡት መጋቢት 1/2008ዓ.ም ሲሆንበአዋጁ መሰረት የአመልካች የስራ ውል ከሚቋረጥበት ነሀሴ 17/2007ዓ.ም በኃላ በመሆኑ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጠ፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሚያዝያ 10/2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ተጠሪ ቀርቦ ባልተከራከረበት ባልጠየቀው ዳኝነት አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የኔን አቤቱታ ብቻ መርምሮ መወሰን ሲገባው ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡ ቅሬታቸው ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ውሳኔው እንዲፀና በመጠየቅ መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የጽሁፍ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ክርክሩ በተመራበት ሥርዓትም ሆነ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ስለመኖር አለመኖሩ መርምረናል፡፡

የአመልካች ቀዳሚ ቅሬታ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ቀርቦ ባልተከራከረበት የኔን ክርክር ብቻ መርምሮ መወሰን ሲገባው ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሲሆን አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ማጣራት አድረጎ የወሰነ በመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም እንዲባል ተከራክረዋል፡፡ በመሰረቱ የድሲፐሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳቡን ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚያቀርበው ተገቢውን ማጣራት አድርጎ የምርመራውን ሙሉ ይዘት የሚያመልክት የምርመራ ሪፖርት በማዘጋጀት ስለመሆኑና፤ የምርመራው ውጤት የተከሳሹን ጥፋተኝነት የሚያረጋግጥ ከሆነ የውሳኔ ሃሳቡ ሊወሰድ የሚገባውን የቅጣት እርምጃ ማመልከት እንደሚኖርበት፤ የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች የዲስፕሊን አፈፃፀምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት ለመደንገግ ከወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 77/1994 አንቀፅ 19 እና 49 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም በስር አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ክርክር ተጠሪ ቀርቦ ያልተከራከረ ቢሆንም አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሚመረምረው የዲሲፐሊን ኮሚቴው ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር አንጻር የሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን እና ያለመሆን ጋር በማገናዘብ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 347 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ተጠሪ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ቀርቦ ባይከራከርም ለዲሲፐሊን ኮሚቴው ክስ አቅርቦ ያስወሰነው እሱ ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ክርክር በኮሚቴው ውሳኔ ላይ ተያይዞ እንደሚገኝ አጠያያቂ ካለመሆኑም በተጨማሪ ይህንን አስመልክቶ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት በተመለከተ የፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 42(5) መሰረት ሰራተኛው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት እስካላጋጠመው ድረስ መታመሙን ለመ/ቤቱ ማሳወቅ እንዳለበት፣ በዚህ መልኩ መታመሙን ላሳወቀ የሙከራ ጊዜውን ለጨረሰ ሰራተኛ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 42(2) መሰረት ህመሙ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ባሉ ተከታታይ 12 ወር ውስጥ ለ8 ወራት ፍቃድ ሊሰጥ እንደሚገባ እና በዚሁ አንቀጽ ንኡስ

አንቀጽ (3)ላይም ለመጀመሪው የ3ወር ጊዜ ከሙሉ ደሞዝ ጋር ለሚቀጥለው 3 ወር ጊዜ ከግማሽ ደሞዝ ጋር ለተከታዩ 2 ወር ያለደሞዝ ፍቃድ ሊሰጥ እንደሚገባ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 79(1) ላይ በዚህ ጊዜ ውስጥ ወደ ስራ ለመመለስ ያልቻለ ሰራተኛ በህመም ምክንያት የስራ ውሉ ሊቋረጥ እንደሚገባ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በህመም ምክንያት ስራ ለመግባት ያለመቻላቸውን ለመ/ቤቱ ካሳወቁበት ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ ህጉ እሰሚፈቅደው 8ወር ጊዜ ድረስ በደሞዝ እና ያለደሞዝ ፍቃድ ሊሰጣቸው የሚገባ በመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ ያልተከፈላቸው ደሞዝ ታስቦ እንዲከፈላቸው አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ከወሰነ በኃላ የአመልካች ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄያቸው የቀረበው መጋቢት 1 ቀን 2008ዓ.ም ሲሆን የ8 ወር ጊዜው የሚያበቃው ነሀሴ 16 ቀን 2007ዓ.ም በመሆኑ ጊዜው ካለፈ በኃላ ያቀረቡት ወደስራ ልመለስ አቤቱታ በህጉ ተቀባይነት የለውም በማለት

የሰጠው ውሰኔ እና ይህንን ውሳኔ በትእዛዝ በማጽናት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያስችል የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ነጥብ ሳይኖር ይህ ችሎት የአመልካችን ቅሬታ የሚቀበልበትን መሰረታዊ ምክንያት አላገኘም፡፡

በመሆኑም ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት ይግባኙን በመሰረዝ የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 044/2009 ጥር 30 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 138065 መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትዕዛዝ የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. አመልካች ጊዜው ካለፈ በኃላ ያቀረቡት ወደ ስራ ልመለስ አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ በተሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ. 19519

ሰኔ 03 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች:-

ፀጋዬ ወርቅአየሁ

ጌትነት መንግስቴ

ሰለሞን ጎራው

ሃብታሙ ውለታው

ኃ/ማርያም ሞገሥ

አመልካች .......... ወርቁ ተገኘ

ተጠሪ .......... የባህር-ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት

መዝገቡ ያደረው ለምርመራ በመሆኑ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

### ፍ ር ድ

ከመዝብ ምርመራው እንደተረዳነው አመልካች ታህሣሥ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የይግባኝ አቤቱታ የባህር-ዳር ከተማ አስተዳደር የቦታ አቅርቦት የሥራ ሂደት ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በወራሚት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሆድ ገበያ ተብሎ ከሚጠራው ሥፍራ በ1989 ዓ.ም የወላጅ አባቴ የነበረውን እና በ1996 ዓ.ም በስሜ የተመዘገበልኝን

በምስራቅ ያረጋል ሙጬ

በምዕራብ መንገድ

በሰሜን አወቀ ከበደ

በደቡብ ምትኬ ምግባር

የሚያዋስኑትን አንድ ቃዳ ተኩል መሬት ለኢንቨስትመንት ይፈለጋል ተብሎ ሲወሰድ ካሣ እንዲከፈላቸው በተደረገው የጥናት ዝርዝር ውስጥ ስማችሁ አልተካተተም በሚል ካሣ ሊከፈልህ አይገባም ተብሎ የተወሰነብኝ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ካሣ እንዲከፈለኝ ይወስንልኝ በማለት ቅሬታውን ለባህር-ዳር ከተማ አስተዳደር የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡

የባህር-ዳር ከተማ አስተዳደር የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ያስቀርባል ብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት አድርጓል፡፡

በዚሁ መሠረት ተጠሪው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት በ1989'ም ሆነ በ1996 ዓ.ም በአመልካች ስም ያልተመዘገበ እና በህገ-ወጥ መንገድ የያዘው ስለሆነ ካሣ ሊከፈለው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ያቀረበው የ1996 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ከዋናው ጋር ያልተገናዘበ፤ የግብር ደረሰኞችም ለየትኛው መሬት እንደተከፈለ የማያረጋግጡ በመሆኑ የአመልካች መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፤ የይዞታ ማረጋገጫ ሊሆኑትም አይችሉም በማለት የከተማው አስተዳደር የቦታ አቅርቦት የሥራ ሂደት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን በቂ ማስረጃ እያለኝ፣ ማረጋገጥም እየተቻለ ተገቢው ማጣራት ሳይደረግ ካሣ ሊከፈልህ አይገባም መባሌ ሥህተት ስለሆነ የሥር ፍርዱ ይሻርልኝ፤ በቂ የሆነ ካሣ እንዲከፈልም ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡ ክርክሩም በዚሁ ተጠናቋል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በግራ ቀኙ መካከል የቀረበውን ክርክር ከማየታችን በፊት የባህር-ዳር ከተማ አስተዳደር የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ለመወሰን ሥልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም የሚለውን ማየት አስፈላጊ ሆኖ በማግኘታችን እንደሚከተለው አይተነዋል፡፡

እንደሚታወቀው ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚወሰዱ የይዞታ ቦታዎችን በተመለከተ ባለይዞታዎች የሚኖራቸውን መብት እና አፈፃፀሙ ምን መምሰል እንዳለበት ለመግዛት የወጣው አዋጅ ቁጥር 272/94 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 16 (3) ላይ እንደተደነገገው የይዞታ ቦታቸውን ስለህዝብ ጥቅም እንዲለቁ የሚወሰንባቸው ሰዎች ማስጠንቀቂያ ሲደርሳቸው በመጀመሪያ ትዕዛዙን ለሰጠው ክፍል፤ ውሳኔው ያልተሻሻለላቸው እንደሆነም ትዕዛዝን ያስተላለፈው አካል

በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካላቸው በአዋጁ አንቀጽ 18 (1) መሠረት ለከተማ ቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል [አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 18 (3)]፡፡ ጉባኤው ካሣን በሚመለከት በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የሚሰኝ ወገንም ቅሬታውን የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ባለበት ቦታ ለሚገኘው የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያቀርባል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል [አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 18 (4)]፡፡ በከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እና መሬት እንዲለቀቅ ትዕዛዝ በሚያስተላልፈው አካል መሃል የሚገኘው የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንደአግባቡ በክልል ወይም በከተማ መስተዳደር ከፍተኛው የሥልጣን አካል በሚወስነው መሠረት እንደሚቋቋም በአዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 19 (1)]

ተገልጿል፡፡ ይህን ተከትሎም የኢ.ብ.ክ.መ. ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 6/94 አወጥቶ ተመሳሳይ አደረጃጀት በመፍጠር ጉባኤውን አቋቁሟል፡፡ ዝርዝር የአሠራር ሥነ-ሥርዓቱን በተመለከተ ምክር-ቤቱ እንደሚወሰን ተገልጿል [ደንብ ቁጥር 6/94 አንቀጽ 15 (1)፤ (3) እና አንቀጽ 19]፡፡ በዚሁ መሰረት የክልሉ ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር 7/95 በማውጣት ዝርዝር የአሠራር ሥርዓቱን አውጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላም መመሪያ ቁጥር 40/2000 ወጥቶ በሥራ ላይ ውሏል፡፡ ደንቡ በርዕሱ ላይ የከተማ-ቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቋቋሚያ እና የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ መመሪያ የሚል ቢሆንም ዝርዝሩ ሲታይ በደንብ 6/94 አስቀድሞ የተቋቋመውን የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመመሪያ በማቋቋም እና ስያሜውንም ሠርዞ የመሬት-ነክ አቤቱታ ሰሚ ጉባኤ የሚል አዲስ አደረጃጀት ፈጥሯል፡፡ እዚህ ላይ አንድ ችግር አለ፡፡ ደንብ ቁጥር 6/94 አስቀድሞ ያቋቋመውን የከተማ-ቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መመሪያው እንዳልተፈጠረ በመቁጠር በስያሜውም አዲስ አደረጃጀት ይፈጥራል፡፡ ይሁን እና መመሪያው ዝርዝር የአሠራር ሥነ-ሥርዓቶችን ከማውጣት ባለፈ በደንቡ የተፈጠረውን ተቋም እንዳልነበረ በመቁጠር በስያሜ አዲስ ተቋም መፍጠሩ በህጎች አደረጃጀት የሥልጣን እርከን የተፈቀደ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ መመሪያው የህጎች የሥልጣን ዕርከን ከሚፈቅድለት በላይ የተራመደ ሆኖ አግኝተነዋል (ultra-virus)፡፡ ስለሆነም በዚህ ነጥብ ላይ መመሪያው ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በደንቡ የተቋቋመው የከተማ ቦታ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አሁንም እንዳለ የሚቆጠር ይሆናል፡፡

የዚህ ተቋም በተግባር አለመኖር ሰዎች መብቶታቸውን በአግባቡ ለማስከበር ዕንቅፋት ሊፈጥርባቸው እንደሚችል ይታወቃል፡፡ እንዲህ ሲሆን ተቋሙ ተግባራዊ ሥራውን እንዲያከናውን ለማድረግ ኃላፊነት ያለበትን ክፍል አግባብ ባለው መንገድ በመጠየቅ መብቶቻቸውን ማስከበር የሚገባቸው ይሆናል፡፡ ይህን ከማድረግ ባለፈ በተግባር የተቋሙን አለመኖር ምክንያት በማድረግ ብቻ ሰዎች በመሬት ጉዳይ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ትዕዛዝ በሚያስተላልፈው አካል እና በከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መሃል በካሣ መጠን ብቻ ሳይሆን በፍሬ ጉዳይ ላይም ይግባኝ ሊሰማ የሚችለውን ክፍል በመዝለል ጉዳዮቻቸውን ለከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡ የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የከተማ-ቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች መከለሥ በመሆኑ በዚህ ጉባኤ የተሰጠ ውሳኔ ሳይኖር የይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑን ሊገለገልበት አይችልም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የአስተዳደሩ አካል የሰጠውን ውሳኔ የሚከልስበትን ሁኔታ ይፈጠራል ወይም ቦታቸውን የሚያጡት ሰዎች በፍሬ ነገር ረገድ በህገ-መንግስቱ የተሰጣቸውን የይግባኝ መብት ያጣሉ፡፡ ስለሆነም የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ ሳይኖር የቀረበለትን ጉዳይ በቀጥታ በይግባኝ የማየት ሥልጣን የለውም፡፡

መመሪያ ቁጥር 40/2000 ተቀባይነት አለው ቢባል እንኳ የአመልካች ቅሬታ ለከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት መመሪያው እንደሚለው ለመሬት-ነክ አቤቱታ ሰሚ ጉባኤ

ቀርቦ ሊታይ የሚገባው ይሆናል፡፡ የዚህ ክፍል በተግባር አለመደራጀት የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በህግ በግልጽ ከተሰጠው ሥልጣን በላይ ያልተደራጀውን ክፍል ሥልጣን ሡብስቦ እንዲይዝና እንዲሠራበት የሚፈቀድበት የአሠራር ሥርዓት የለም፡፡ ስለሆነም በሁለቱም መንገድ ቢሆን የባህር-ዳር ከተማ አስተዳደር የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የአመልካቾች ቅሬታ በተጠቀሱት ክፍሎች ላይ ቀርቦ ከመስተናገዱ በፊት ከአስተዳደሩ ውሳኔ የአመልካችን ቅሬታ በቀጥታ ተቀብሎ መወሰኑ ከፍ ሲል በተጠቀሱት ምክንያቶች ከሥልጣኑ በማለፍ የሰጣቸው በመሆኑ ውሳኔው የሚጸና አይደለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለውንም ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

የባህር-ዳር ከተማ አስተዳር የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የአመልካች ቅሬታ በጉባኤ ከመታየቱ በፊት በቀጥታ ተቀብሎ በማስተናገድ ውሳኔ መስጠቱ ከሥልጣኑ በማለፍ የሠራው (ultra-virus) በመሆኑ ውሳኔው የሚጸና አይደለም፡፡ ስለሆነም የከተማ-ነክ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ ሽረናል፡፡ ኪሣራ እና ወጪ ይቻቻሉ፡፡

**ትዕዛዝ**

የተሰጠ ዕግድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡